በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከማርች 11-20፤21-31/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

**እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ** ........ - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ........ - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 3 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20, 2024 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ - 7 -

እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ - 7 -

ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከማርች 21-31፣ 2024........ - 8 -

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 8 -

እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -

እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት የማርች አስር ቀናቶች በመካከለኛው፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 18.5 እና 2.8፣ በአርባ ምንጭ 5.2 እና 1.2፣ ሃዋሳ 19.7፣15.4፣5.3 እና 9.0፣ በኮምቦልቻ 12.7፣16.7፣17.4፣18.1 እና 22.3፣ በደብረ ማርቆስ 6.0፣1.7፣6.5 እና 6.0፣ በቢሾፍቱ 9.8፣1.8 እና 30.2፣ በድሬ ዳዋ 14.2፣2.9 እና 0.8፣በጎሬ 39.8፣2.3፣6.7 እና 2.6፣ በጅማ 15.0፣1.0፣4.1፣3.3 እና 10.8፣ በመቀሌ 8.4፣ በመተሃራ 12.0፣ በነቀምቴ 25.9፣1.6 እና 7.8፣ በባሌ ሮቤ 14.5 እና 1.0፣ በአቦምሳ 4.7፣1.5 እና 13.5፣ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 13.7፣19.0፣0.8 እና 5.6፣ በአደሌ 5.1፣ በሀሮማያ 12.1፣ በአለም ከተማ 3.5 እና 10.5፣ በአማን 11.2፣9.6፣3.6፣13.8 እና 6.8፣ በአምባ ማሪያም 11.4፣11.3፣9.6 እና 16.8፣ በአምቦ 10.5፣8.8 እና 31.5፣ በአምደወርቅ 4.2፣5.1 እና 34.0፣ በአንገር ጉቲን 4.2፣ በአርጆ 2.6፣18.6፣4.6፣2.4 እና 22.4፣ በአርሲ ሮቤ 8.1 እና 9.5፣ በአፅቢ 6.0፣ በአዋሽ አርባ 3.5፣ በባቲ 32.0፣ በበደሌ 1.2፣6.6፣2.7 እና 7.6፣ በብላቴ 3.2፣2.9፣1.8 እና 3.8፣ በቦሬ 12.0፣7.8 እና 2.0፣ በቡኢ 2.7፣17.8፣31.6 እና 33.5፣ በቡርጂ 10.0 እና 0.8፣ በጨፋ 11.0፣7.8 እና 5.6፣ በጭፈራ 8.7 እና 6.4፣ በጭራ 9.6፣11.8፣8.1 እና 2.6፣ በደብረ ብረሃን 5.7፣4.3፣6.4 እና 1.2፣ በደብረ ታቦር 1.2፣ በደብረ ወርቅ 30.9 እና 3.0፣ በደምቢ ዶሎ 7.4፣ በዲላ 10.6፣3.7፣6.5 እና 7.0፣ በዶሎመና 30.7 እና 7.4፣ በኢጃጂ 10. እና 1.2፣ በእንዋሪ 1.5፣1.4፣3.8 እና 16.0፣ በፍቼ 1.8፣3.5፣8.2፣32.4 እና 4.4፣ በፉኚዶ 8.1፣ በጋቲራ 15.4 እና 12.8፣ በግዮን 9.2፣4.6፣7.8 እና 16.0፣ በጉንዶ መስቀል 24.0፣1.4፣5.2 እና 8.2፣ በቡሌ ሆራ 7.2 እና 3.2፣ በሀረር 3.7፣41.7 እና 9.5፣ በሆሳና 12.0፣29.3፣2.5፣42.0፣12.0 እና 25.5፣ በእምድብር 26.4፣4.2፣5.5፣3.1፣3.3 እና 12.2፣ በጃራ 1.2 እና 2.6፣ በጂንካ 1.4፣1.5 እና 2.6፣ በካቺሴ 14.7፣2.0፣6.0 እና 6.3፣ በኮንሶ 12.5 እና 22.8፣ በቁሉምሳ 10.5፣2.4፣4.6 እና 4.7፣ በላሊበላ 3.9፣7.8 እና 1.5፣ በሊሙገነት 1.5፣1.1፣4.1፣44.7 እና 2.0፣ በማይጨዉ



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

15.5፣2.3፣1.2 እና 2.5፤ በማጂ 20.0፣10.0 እና1.2፤ በማሻ 34.6 እና 30.0፤ በመሃልሜዳ 2.5 እና 3.9፤ በሚኤሶ 6.7፣15.7 እና 1.2፤ በመካነሰላም 9.8 እና 2.8፤ በምዕራብ አባያ 2.2 እና 3.0፤ በሞያሌ 15.5፣1.8 እና 24.3፤ በአዳማ 1.9፣54.1፣1.4 እና 13.5፤ በንፋስ መዉጫ 25.1 እና 4.7፤ በኑራኤራ 6.4፤ በሳዉላ 1.5፣13.5፣15.2 እና 6.2፤ በሰኮሩ 16.5፣7.2፣3.6 እና 8.2፤ በስንቃጣ 5.5 እና 31.9፤ በሻምቡ 13.3 እና 6.2፤ በሾላ ገበያ 10.0፤ በሲርንቃ 3.3፣26.5 እና 3.5፤ በቴፒ 1.8፣2.3፣5.3 እና 14.2፤ በተርጫ 19.2፣14.7፣16.8፣1.2 እና 48.9፣ በፅፅቃ 2.0 እና 5.2፤ በወገልጤና 7.0 እና 6.2፤ በወራቤ 14.7፣5.1፣10.9 እና 1.0፤ በወላይታ ሶዶ 5.0፣1.6፣3.9፣6.3 እና 1.6፤ በያበሎ 3.9፣6.3 እና 1.6፤ በየትኖራ 9.9፣1.811.4 እና 1.9፤ በባቢሌ 5.1፣በጭናክሰን 3.5፣ በጎብሬ 4.6 እና 2.4፤በአደዉ 10.2፤ በካራሚሌ 9.2፤ በጨለንቆ 4.3፣3.4፤በዉጫሌ 48.0፤ በቀብሪ በያ 4.6፤ በለፈሳ 1.2፤ በአርታክ 10.2፣ በኤረር 30.6፣ በኩረፋ ጨሌ 23.7፣ በሀዴዉ 10.2 እንዲሁም በባቱ 5.2፣2.5፣9.0፣13.4 እና 21.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ቄለም ወለጋ፣ኢሉባቦር፣ጅማ፣ቡኖ በደሌ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣የሲዳማ ክልል እና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ንዌር እና ማዠንግ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣አሶሳ እና ካማሺ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋህግምራ፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ሰሜን፣ምዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ሰሜን ሸዋ፣ ከአፋር ክልል ዞን 2፣3፣4 እና 5፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ማዕከላዊ፣ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ጀረር፣ኖጎብ፣ቆራሄ፣ሸበሌ፣አፍዴረ፣ሊበን እና ደዋ ዞኖች፤ሀረሪ፣ድሬ ዳዋ እና አዲስ አበባ ላይ ከ120-160 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ደቡብ ምስራቅ፣ማዕከላዊ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣4፣5 እና 3፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ፋፋን፣ጀረር፣ኤረር፣ኖጎብ፣ቆራሄ፣ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ዞኖች፤ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ዋግህምራ፣የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ምስራቅ ጎጃም፣ሰሜን ሸዋ፣ሰሜን፣ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና፣ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ጅማ፣ኢሉባቦረ፣ቡኖ በደሌ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካማሺ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ሁሉም የሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ሀረር፣ድሬ ዳዋ እና አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-43 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይና እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፉ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተለይም በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን በተለይም በሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች የነበረው እርጥበት ቀደም ብለው ተዘርተው በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙትም ሆነ በመዘራት ላይ ላሉ ሰብሎች የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ምስራቃዊ አባይ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ በጥቂት የላይኛው  ዋቤ ሸበሌ እና ተከዜ እንዲሁም የላይኛው እና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት  ነበራቸው (ካርታ 5)




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ-ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የወቅቱ ዝናብ አብዛኛውን የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚሸፍን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ ያገኛሉ፡፡


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት ይበልጥ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7 )፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የመካከለኛዉ እና የሰሜን ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የዋግህምራ ዞኖች፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ እንዲሁም የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፤ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፤ የቦረና ዞን፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛዉ፣ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የፋፈን፣ የዳዋ፣ የሊበን እና ጥቂት የአፍዴር ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በጋምቤላ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20, 2024 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄደው ከማርች አጋማሽ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በማርች ሶስተኛው አሥር ቀናት አብዛኛዎቹን የበልግ አብቃይና ተጠቃሚ ቦታዎችን ያካተተ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይስተዋልባቸዋል፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 21-31 Mar 2024




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከማርች 21-31፣ 2024

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ቀናት የደቡብ፤ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለበልግ እርሻ ሥራዎች፣ ለአፈር እርጥበት መጠናከርና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚኖረውን በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ጋር በሳምንቱ ውስጥአልፎ አልፎ ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውል ውሃን የመሰብሰብና የማጠራቀም ተግባራት ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በላይኛው እና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ምስራቃዊ አባይ፣ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መሻሻል አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et